EthioLion

ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ
የሰሜን አሜሪካ ድጋፍ አካል
Coalition for Unity and Democracy (KINIJIT)
North America Support Group

10/18/2008

## ከቅንጅት መኢአድ የሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች የተሰጠ የአቋም መግለጫ

በሰሜን አሜሪካ የቅንጅት መኢአድ የድጋፍ ድርጅቶች ከኦክቶበር 17-18 በዋሽንግተን ዲሲ ስብሰባ አካሂደዋል።

የዚህም ስብሰባ ዋና አላማ በሰሜን አሜሪካ አመራሮች መካከል የተፈጠረዉን አለመግባባት መፍትሄ ለማፈላለግ በፓርቲዉ ም/ሊቀመንበር በክቡር አቶ አባነህ ብርሃኑ የተጠራ ሲሆን በርካታ የቻፕተሩ አባላት በስብሰባዉ ተገኝተዋል።ሆኖም ግን የሰሜን አሜሪካ የስራ አስፍፃሚ አባላት በስብሰባዉ ቦታ ሳይገኙ ቀርተዋል።

ክቡር አቶ አባይነህ ብርሃኑ ፓርቲዉ የሚገኝበትን ከፍተኛ ደረጃ ለቻፕተር ተምካዮች ካስርዱ በኋላ በሰሜን አሜሪካ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች ላይ ያለዉን ደካማ የስራ እንቅስቃሴ በማያሻማ መልኩ በማስርዳት ፓርቲዉንም በጣም እንዳሳዘነ ገልጠዋል።

ጉባኤዉም ሰፋ ያለ ጊዜ ወስዶ የቻፕተሮችን የስራ እሪፖርት ካዳመጠና የሰሜን አሜሪካ የስራ አስፍፃማዎች ላይ የቻብተር ተዎካዮች ያላቸዉን ቅሬታ ከመረመረ በኋላ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ድክመቶችን ተመልክቶአል።

1.የሰሜን አሜሪካ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከፌብሪዎሪ 14/2008 ጀምሮ እስካሁን ድረስ የአደረጋቸዉ የስራ እንቅስቃሴዎች ድርጅቱን ከማጠናከር እና ገንዘብ ከማሰባሰብ ይልቅ በተለያዩ የእርስ በርስ ሹክቻዎች ላይ ጊዜአቸዉን ያጠፉ በመሆናቸዉ።
2.የቻፕተሮችን መተዳደሪያ ደንብ በ90 ቀን ዉስጥ በቻፕተሮች ተሳትፎ ተሻሽሎና ፀድቆ ስራ ላይ እንዲዉል በማድረግ ፍንታ አዲስ መተዳደሪያ ደንብ የአወጡ በመሆናችዉ።
3.የድርጅቱ አባላትን ከድርጅቱ ደንብና መመሪያ ዉጭ ከአባልነት የአስዎገዱ በመሆነቸዉ።
4.በፓርቲዉ መሪዎች ላይ የፈጠራ ወሬ ከማስወራታቸዉም በላይ ስማቸዉን በማጉደፍ ስራ ላይ መሰማራታቸዉ በመረጃ የተደረሰበት በመሆኑ።

5.ከፓረቲዉ ም/ሊቀመንበር ከክቡር አቶ አባይነህ ብርሃኑ ለቀረበላቸዉ ጥሪ ከእምቢተኛነታቸዉም በላይ እንደማይገነኙ በአቋም መግለጫ የገለጡ በመሆናቸዉ።

ከተራቁተጥር 1-5 በተዘረዘሩት እና በሌሎች ግድፈቶች ምክንያት ይህ ጉባኤ የሰሜን አሜሪካ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን አሰናብቶአል። በምትካቸዉ ሌላ እንዲያስመርጡ 9 አባላት ያሉበት አስመራጭ ኮሚቴ ኦክቶበር 18/2008 ኢ.ም ተቋቁሞአል ይህ መግለጫ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ስራዉን እንዲጀምር ተወስኖአል። በመሆኑም በአቶ ግዛዉ ተስፋየ የሚመራዉ ኮሚቴ ድርጅታችንን የማይወክል መሆኑን ጉባኤዉ በአንድ ድምፅ ወስኖአል።በተጨማሪም በተወገደዉ ኮሚቴ አፍራሽ ቅስቀሳና በመረጃ እጦት ምክንያት ድርጅታችሁን ከመርዳት የተቆጠባችሁ አባሎቻችን በሙሉ የተለመደዉን ድጋፋችሁን እንድታደርጉ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ

1629 K Street, NW Suite 300, Washington, DC 20006
Tel: (202)565-7864, Fax: (202)331-3759

Ethiopia will Prevail !

EthioLion.Com